# ዋ! ብሎ መለየት

በረኸሙ አልመው እየገሰገሱ
ግን ደግሞ ሳይደርሱ
ካሰቡት ዓላማ  ብዙ ሲቀራቸው
በጉዞ ላይ ሳሉ ዕድሜ እየከዳቸው
ላመኑበት ዕምነት እየሆኑ ቤዛ እየተሰበሩ
ስንቱ አፈር ለበሱ ስንቱ ተቀበሩ።

የኢህአፓ ልጆች እነ ሞት አይፈሬ
አሁን መጡ ሲባል ከትናንት ዛሬ
ስንቶች እረገፉ እንደ ሾላ ፍሬ
ስመ ጥር አርበኞች ገናና ገናና
እንደ ሰው ወደቁ ሁሉም ሰው ሆኑና።

ሰው ሆነው ተፈጥረው
ሞትን ካዳም ወርሰው
ሀዘንና ፀፀት ከኋላ እየጣሉ
ሁሉም ሞትን ሞቱት በህይዎት እያሉ።

ምን ቀራጥ ቢሆኑ ምንም ቢጀግኑ
እየገፉ ሲሄድ እየመሸ ቀኑ
ዋ! ብሎ መለየት እንደ ሙሉጌታ
ሰው መሆን አይቀርም አፈር ላይ ምኝታ።

ሚያዚያ 2007

አብርሃም በየነ